# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 297 ጥር 9 2006 ገጽ 1


ወያኔ ፈርቶአል ተረብሾአል። ስለዚህም ኢሳትና አሁን በአክራሪ ድርጅቶች ልሳንነት የተፈረጁት የአገር ውስጥ ህትመቶች ከምርጫው በፊት መጥፋት ይኖርባቸዋል። ያ ካልሆነ በመላው አገሪቱ የሰፈነው የሥልጣን ብልግናና የሃብት ዘረፋ የፈጠረው የኑሮ ውድነት ያስመረራቸው ሚሊዮኖች የመጪውን ምርጫ ውጤት አስታከው ሆ ብለው አደባባይ ሊወጡና የአገዛዙን የሥልጣን እድሜ ለማሳጠር ተቃዋሚዎች ለሚያካሄዱት ትግል መሳሪያ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ተፈርቶአል። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ ለ2007ቱ ምርጫ የመንግስት ሰራተኞችን በደመወዝ ማሻሻያ ለመደለል እየሞከረ መሆኑ ተሰማ

ፋሽስት ወያኔ ሁል ጊዜም ከምርጫ በፊት ለምስኪኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማይፈጸሙ ቃሎችን በመግባት የታወቀ ሲሆን በመጪው ዓመት ለሚያደርገው የይስሙላ ምርጫ ያግዘው ዘንድም ለመንግስት ሰራተኞች የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ለማድረግ እንዳሰበ በሰፊው እያስነገረ ይገኛል። የወያኔን አካሄድ ስላልደገፉና ተለጣፊ መሆን ስላልፈለጉ ብቻ ባንድ ጊዜ ካርባ በላይ ፕሮፌሰሮችንና ሌሎችንም በሽዎች የሚቆጠሩ ባለሙያዎችን በአገዛዝ ዘመኑ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ወይም ደግሞ በብቃት ማነስ እያለ ሲያባርር የነበረው ዘረኛው ወያኔ ዛሬ ተገልብጦ "የሰራተኞች ፍልሰት በደመወዝ ማነስ የተነሳ ነው" በማለት ለመንግስት ሰራተኞች የሚያስብ በመምሰል ማባበል እንደያዘ እየተሰማ ነው።

በአነስተኛ ወርሃዊ ክፍያ ምክንያት ኑራቸው ድሮም እንደነገሩ የነበሩት የኢትዮጵያ የመንግስት ሰራተኞች ይቅርና ጥሩ ገቢ ያገኛሉ፣ ልጆቻቸውንም በመልካም ሁኔታ ያሳድጋሉ፣ ያማረ ኑሮም የገፋሉና የመሳሰሉትን ሲባሉ የነበሩት በንግዱ መስክ የተሰማሩት ወገኖች ፋሽስት ወያኔ በፈጠረው የኑሮ ውድነት የተነሳ ከሰው በታች ሆነው መታየት ከጀመሩ የቆዩ ቢሆንም

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ ቀጣዩን ምርጫ በሥልጠና ስም የግል ንብረቱ ለማድረግ ዝግጅቱን አጠናቀቀ

ፋሽስት ወያኔ የአፈና መዋቅሩን ለመዘርጋት መረጃ በመሰብሰብ የሚጠቀምባቸውን ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ሰራተኞችን ጨምሮ ሌሎች የወያኔ አመራሮችን በጸረ ሽብር ግብረሃይል ስልጠና ማካተቱ ተሰማ። የ1997 ዓ/ም የምርጫ አፈና ተሞክሮው እየተጠቀሰና ከወያኔ ፕሮፓጋንዳነት በቀር ታይተው የማያውቁ የሽብር ችግሮች ድንገት ቢፈጠሩ በሚል መላ ምት እንዴት በቁጥጥር ስር ማዋል እንደሚቻል ያጠቃለለ ነው ተብሏል ስልጠናው።

በቀጣይ ይህንኑ ስልጠና በስፋት ለማካሄድና ሰፊውን ሕዝብ የዚሁ ስልጠና አካል ለማድረግ ከፍተኛ ዝግጅት እየተደረገ ሲሆን ከወያኔ በቀር ምንም ሽብርተኛ በማይታይባት ኢትዮጵያ ሁሉም ሕዝብ ካሁኑ የሌለ ሽብርተኛ ፍለጋ ላይ እንዲሰማራ ከፍተኛ ዘመቻ ተጀምራል ተብሏል። ሕዝብ በሀገሩ ስርቶ እንዳይበላ፣ በሰላም ወጥቶ እንዳይገባ፣ ሰላማዊ ኑሮውን በተረጋጋ ሁኔታ እንዳይመራ በማድረግ ላይ ያለው ወናውና ትልቁ ሽብርተኛ ፋሽስት ወያኔ ሆኖ እያለ ራሱ ተገልብጦ የሌለ ሽብርተኛ እፈልጋለሁ እያለ በስልጠና በማመካኘት ሕዝብ በማመስ ላይ ይገኛል ተብሏል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ወያኔ በሶማሊያ ክልል 47 ሰዎች መግደሉ ተሰማ

የወያኔ ቅጥረኛ በሆነዉ የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንትና በጄኔራል አብርሃም የሚመራዉ የክልሉ ልዩ ሚሊሺያ ጦር ባለፈዉ ታህሳስ ወር በህዝብ ላይ በከፈተዉ ተኩስ ህፃናትንና ወጣቶችን ጨምሮ 47 ሰዎች መግደሉን የክልሉ የአገር ሽማግሌዎች የሟቾቹን ስም ዝርዝር በመጥቀስ ለኢትዮጵያ ሳቴላይት ሬድዮና ቴሌቪዥን በላኩት መልዕክት ገለጹ። የክልሉ ልዩ ሚሊሺያ በሚል ስያሜ የሚታወቀዉና ሆን ብሎ ዜጎችን ለማጉላላት፤ ለማሰቃየትና ለመግደል የተመሰረተዉ ይህ ነብሰ ገዳይ ኃይል በትምህርት ገበታቸዉ ላይ በነበሩ ተማሪዎች ላይ ጭምር ተኩስ ከፍቶ ህጻናት ተማሪዎችን መግደሉን የአይን ምስክሮች ተናግረዋል። ይህንን የጭካኔ ግድያ በተመለከተ በቀላፎ አካባቢ የሚኖሩ የየረር ባሬ ጎሳ የአገር ሽማግሌዎች ለጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ በላኩት መረጃ የፌደራሉ መንግስት በአስቸኳይ ደርሶ እንዲታደጋቸውም ጠይቀዋል።

አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የጠየቁ የኢህአዴግ ባለስልጣን በሰልክ ሰለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት መረጃ፤ ግድያዉ የተፈጸመበት አካባቢ ህዝብ የክልሉ መንግስት ጭቆና ያደርስብናል በማለት ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ሲጠይቁ የነበረ በመሆኑ የተፈጸመባቸዉ የጅምላ ግድያ እንዳላስደነቃቸዉ ተናግረዋል።

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የኢትዮጵያ አርሶ አደር በወያኔ ላይ አይነሳም ሲል በረከት ስምኦን አላገጠ

መተካካት የሚሉት የወያኔ ፈሊጥ በፍጹም የማይመለከተዉ ምላሰ ረጂሙ በረከት ከሰሞኑ ለመንግስት ሚኒስትሮችና ለከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣኖች በተዘጋጀው የምርጫ ውይይትና ግምገማ ላይ ባደረገዉ ንግግር ላይ የኢትዮጵያ አርሶ አደር እስካሁን በተደረገለት ስራ በሚገባ የረካ ስለሆነ " መንግስት ሰላማዊ ሰልፍ ውጣ ቢለው ይወጣል፣ መንግስት ተኛ ቢለው ይተኛል፣ ግፍ ብንፈጽም እንኳን አርሶ አደሩ ይህንን መንግስት ይሸከመዋል እንጂ ምንም አይለውም፣ በማለት ሃያ አመት ሙሉ መሬቱን ተቀምቶ በተገፋዉ የኢትዮጵያ አርሶ አደር ላይ ማላገጡን ከወደ አዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ።

ይህ ኢትዮጵያ ለምትባል አገርና ለኢትዮጵያ ህዝብ ምንም ግድ የሌለዉ ቦዘኔ፤ መሬቱ ተቀምቶ ለባዕዳን የተሰጠበት የኢትዮጵያ ገበሬ በጨቋኞች ሲረገጥና ሲበደል ደስ የሚለዉ ይመስል ገበሬዉ ብዙ ተደርጎለታልና ብንረግጠዉም ይሸከመናል ሲል የተለመደዉን የዕብሪተኝነት ንግግሩን አድርጓል። በረከት ስምኦን ምንም የማይገባዉ ጭንቅላተ ድንጋይ ሆኖ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ አርሶ አደር እንኳን መሬቱን እየቀማ ለባዕዳን የሚሰጠዉን ወያኔን የመሰለ ዘረኛ መንግስት ከፊዉዳሊዝም ነጻ አዉጥቼሀለሁ ብሎ ሲፎክር የነበረዉን ደርግም አልተቀበለዉም። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ኢህአዴግ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መመሪያን መተውን አስታወቀ

ከጌታዉ ከመለስ ዜናዊ ጋር ሆኖ እነሱ እራሳቸዉ ምን እንደሆነ በዉል ለይተዉ የማያዉቁትን አብዮታዊ ዲሞክራሲን ኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባ ላይ የጫነዉ በረከት ስምኦን አገርን ለመምራት የምንከታቸዉ ፍልስፍናዎች ወቅቱን ተከትለዉ የማይሻሻሉ ከሆነ ይዝጋሉ በማለት አብዮታዉ ዲሞክራሲ ብቻ ሳይሆን ይህንን እንደግዳ ፍልስፍና ተሸክመዉ ያመጡት ሰዎችም የዛጉና ግዜ ያለፈባቸዉ መሆኑን አመነ። በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያምን የማማከር ሃላፊነት ተሰጠዉ በረከት ስምኦን ከወያኔ ባለስልጣኖች፤ሚኒስትሮችና ከኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ባደረገዉ ውይይትና ግምገማ " ህዝቡን ለመምራት የሚነደፉ ንድፈ ሀሳቦች ( ቲዮሪዎች) በየጊዜው ካልተሻሻሉ የሚዝጉ በመሆናቸው አብዮታዊ ዲሞክራሲ በልማታዊ ዲሞክራሲ እንዲተካ ተደርጓል ብለዋል። የኢህአዴግ መንግስት ይበልጥ የሚገለጸው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ሳይሆን በልማታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ነው በማለት በረከት ስሞኦን የፍልስፍና ለዉጡን ይፋ አድርጓል። አብዮታዊ ድሞክራሲም ሆነ ልማታዊ ዲሞክራሲ ምን እንደሆኑና ለምን እንደሚጠቅሙ ተጠንቶ የተቀመጠ ምንም አይነት የጽሁፍ መረጃ እንደሌለ የሚታወቅ ሲሆን በረከትም ሆነ መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ግዜ አብዮታዊ ዲሞክራሲ መመሪያችን ነዉ ከማለት በቀር አንድም ቀን ምን ሰለመሆኑ የተናገረዉ ንግግር እንዳልነበረ የሚታወስ ነዉ።

እንደ በረከት ሰምኦን አባባል አብዮታዊ ዲሞክራሲ በልማታዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት ከመተካቱ በፊት ፣ ኢህአዴግ ለ3 ተከፍሎ ነበር። አንደኛው የአመራር ወገን "ችግራችን የውስጥ ነው እና በቅድሚያ የውስጥ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ ዘረኛዉ የወያኔ ዘገዛዝ የሽብር ግበረሀይሉን ወደ ተለያዩ የአማራ ከቶሞች ሊልክ መሆኑ ተሰማ

የሕወሓት መራሹ የወያኔ አገዛዝ የሽብር ግብረሃይል ቡድን በአማራ ክልል የተለያዩ ከተሞች የሽብር ተግባር የመፈጸም እቅድ እንዳለው መረጃ ይፋ የሆነው በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት ነው።ይህ ይፋ የሆነው መረጃ እንደሚጠቁመው ካለፈው ሳምንት ጀምሮ በተለያዩ የአማራ ከተሞች አሸባሪዎች ሰርገው ገብተዋል የሚል ፕሮፓጋዳ በወያኔ ሕውሃት አማካኝነት በመነዛት ላይ ሲሆን በሕዝባዊ አገልግሎት ስራ የተሰማሩ ዜጎችን በማዋከብ ናቸው።

ህወሃት የራሱን አሸባሪ ቡድን የደህንነት አባላት በዝውውር ከሶማሊያ በማስመለስ ወደ ባህር ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ እና ሌሎች የአማራ ክልል ከተሞች የመደበ ሲሆን ተልዕኳቸውም በከተሞቹ የሽብር ተግባር መፈጸም እና ግርግር መፍጠር ነው። የሽብር ተግባሩ ከተፈጸመ በኋላ በአካባቢዎቹ የሚገኙ እና አገዛዙን ያሰጋሉ የተባሉ ግለሰቦችን በአሸባሪነት እና በአክራሪነት ስም ለማፈስ እንደታቀደም ምንጮቹ ጠቁመዋል።

## የወያኔን የሚዲያ አፈና ማመከን የጊዜው አጣዳፊ ተግባር ነው

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የአገራችንን በትረ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ ህዝባችን ስለራሱና ሰለአገሩ ምንም አይነት መረጃ ከአማራጭ የመገናኛ ብዙሃን ምንጮች እንዳያገኝ ያሉትን ዕድሎች በሙሉ ድርግም አድርጎ ዘግቶ ኖሮአል።

የወያኔ መሪዎችና ተሿሚዎች በየግላቸው ምንም ቁብ በማይሰጡትና ተቃዋሚዎች እንዲያከብሩት ነጋ ጠባ በሚወተውቱት የአገሪቱ ህገመንግሥት አንቀጽ 29 ዕውቅና ካገኙ የዜግች መብቶች አንዱ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሮአዊ መብት ሆኖ ሳለ እየተካሄደ ያለውን የሥልጣን ብልግናና አገሪቱን እያራቆተ ያለውን ዘረፋ በመተቸታቸው ብቻ በአንድ ወቅት እንደ አሸን ፈልተው የነበሩ የነጻ ጋዜጣ አዘጋጆችና አሳታሚዎች በሽብርተኝነት ተወንጅለው ከፊሉ ከአገር እንዲሸሽ ሌላው አፉን ዘግቶ እንዲቀመጥ አለያም የፈጠራ ክስ እየተመሰረተባቸው እስር ቤት እንዲማቅቁ ተደርገዋል። አሁንም በመደረግ ላይ ናቸው። በወያኔ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽና የዜጎች መረጃ የማግኘት መብት አፈና የአሜሪካና የጀርመን መንግሥታት በየግላቸው የሚያስተዳድሩዋቸው የአሜሪካና የጀርመን ድምጽ ሬዲዮኖች እንኳ ከጥቃቱ ማምለጥ ስላልቻሉ እነሆ እስከዛሬ ያልተቋረጠ የማጥላላት ዘመቻ ይካሄድባቸዋል።

ዜጎች ሃሳባቸውን በነጻነት መግለጽ ከቻሉና ከየትኛውም መዲያ መረጃ የማግኘት መብታቸው ከተረጋገጠ ሥልጣን ላይ ውሎ እንደማያድር ጠንቅቆ የተረዳው የወያኔ አገዛዝ በዚህ የሚዲያ አፈና ተግባሩ በመቀጠል ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥንና ሬዲዮን እንዲሁም ህዝብ አልፎ አልፎ ሃሳቡን ለመግለጽ በሚገለገልባቸው ጥቂት የአገር ውስጥ ህትመቶች ላይ የተለመደውን የጥቃት ጅራፉን ለማሳረፍ ታጥቆ ተነስቶአል። ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ በመረጃና ደህንነት መሥሪያ ቤቱ ተዘጋጅቶ የህወሃት ቀድሞ ታጋዳላዮች በሚቆጣጠሩትና እንደግል ንብረታቸው በሚፈነጩባቸው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የተሰራጨው ዘገባ እንደሚያመለክተው ከአሁን ቦኋላ ማንኛዉም የመንግስት ባለስልጣን፤ የገዢዉ ፓርቲ አባላትና የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ምንም አይነት ቃለመጠይቅ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥንና ሬዲዮ እንዳይሰጡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአል። ማስጠንቀቂያውን ተላልፎ በተገኘ ማንም ሰው ወይም ድርጅት ላይ የአሸባሪነት ወንጀል ክስ እንደሚመሰረትበትም ዛቻና ማስፈራሪያ በተለመደው የቃላት ጋጋታ ተገልጾአል።

ይህ ከሰሞኑ የወያኔ ብሄራዊ መረጃ ደህንነትና ኮሚኒኬሽን መስሪያቤት ያወጣዉ ማስጠንቀቂያ አዘል መግለጫ የሚያሳየን ነገር ቢኖር ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዜጎች የሚናገሩትን ፤ የሚጽፉትን፤ የሚያነቡትንና የሚሰሙትን ብቻ ሳይሆን የሚያስቡትንና ሊደግፉት ወይም ሊቃወሙት ይችላል ተብሎ የሚጠረጠረውን ሁሉ አስቀድሞ ለመቆጣጠር ፍላጎቱ ያለው መሆኑን ነው።

ከሰሞኑ መግለጫ የተለየ ነገር ቢኖር ህዝባችንን በፍርሃት አንገት ለማስደፋት ሲባል የወያኔ ፓርላማ በሽብርተኝነት የፈረጀውን ንቅናቄያችንን ግንቦት 7ንና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥንን በአንድነት የመፈረጅ ስልት ይፋ መደረግ መቻሉ ብቻ ነው።

የወያኔን ቁንጮዎች ጨምሮ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ይገነዘበዋል ብለን እንደምናምነው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥን ኢሳት የተቋቋመው የአገራቸው ጉዳይ የሚያንገበግባቸው ቅን ዜጎች ባዋጡት የገንዘብ መዋጮና በሚሰጡት ያልተቋረጠ የእውቀትና የፋይናንስ ድጋፍ ነው። ተቋሙ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት 22 አመታት በወያኔ የሚዲያ ሞኖፖሊ ተይዞ የኖረውን የአገራችንን አየር ክልል ሰንጥቆ በመግባት ህዝባችን ስለ አገሩና ስለራሱ ጉዳይ በቂ መረጃ እንዲያገኝ በመጣር ላይ ያለ ብቸኛ መገናኛ ብዙሃን ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ ነው።

ሃቁ ይሄ ሆኖ ሳለ ለምንድነዉ ታዲያ ላለፉት ሁለት አመታት ስብህት ነጋን ጨምሮ የተለያዩ የገዢዉ ፓርቲ ቱባ ቱባ ባለስልጣናት ሳይቀሩ በተደጋጋሚ ቀርበዉ በስነ ስርአት የተስተናገዱበትን ይህንን ሚዲያ የወያኔ ፓርላማ ቀደም ሲል በአሸባሪነት ከፈረጀው ንቅናቄያችን ግንቦት 7 ጋር መወንጀሉ ለምን ይሆን ? መልሱ ቀላል ነው። ከአገዛዙ ያልወገኑ ማናቸውም ሚዲያዎች እንደሚያደርጉት ኢሳት ስርጭቱን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ነጋ ጠባ በኢትዮጵያ ቴለቪዥንና ሬዲዮ የሚደሰኮረው ልማትና ዕድገት ተጠቃሚው ሥልጣንን የሙጥኝ ያሉ የቀድሞ ታጋዳላዮችና የቅርብ ዘመዶቻቸው እንጂ ህብረተሰቡ አለመሆኑን በግልጽ ከማጋለጥ ባለመቆጠቡ ጥርስ ውስጥ ገብቶአል። ከዚህም በተጨማር ለምዕራባዊያን ፍጆታና ድጋፍ ማግኛ በየአምስት አመቱ የሚደረገው የምርጫ ተውኔት ወቅት ስለተቃረበ ተቃዋሚዎች አጋጣሚውን ተጠቅመው በዚህ ሚዲያ ያብጠለጥሉኛል፤ የስልጣን ብልግናውንና የሙስናውን ጉዳይ ይዘከዝኩታል የሚል ፍርሃትና ስጋትም አለው። በእርግጥ ዝክዘካው በይስሙላ ምርጫው ላይ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ እኛ የጉዳዩ ባለቤቶች ቀርተን ምዕራባዊያን ለጋሾችም አያጡትም። ሆኖም ግን ወያኔ ፈርቶአል ተረብሾአል። ስለዚህም ኢሳትና አሁን በአክራሪ ድርጅቶች ልሳንነት የተፈረጁት የአገር ውስጥ ህትመቶች ከምርጫው በፊት መጥፋት ይኖርባቸዋል። ያ ካልሆነ በመላው አገሪቱ የሰፈነው የሥልጣን ብልግናና የሃብት ዘረፋ የፈጠረው የኑሮ ውድነት ያስመረራቸው ሚሊዮኖች የመጪውን ምርጫ ውጤት አስታከው ሆ ብለው አደባባይ ሊወጡና የአገዛዙን የሥልጣን እድሜ ለማሳጠር ተቃዋሚዎች ለሚያካሄዱት ትግል መሳሪያ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ተፈርቶአል። ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከብዙ የወያኔ ጥቃትና አፈና ተርፈው አገር ውስጥ በመታተም ላይ በሚገኙ 8 መጽሄቶች እና ለኢትዮጵያዊያን ብቸኛ የመረጃ ምንጭ ሆኖ በማገልገል ላይ በሚገኘው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥንና ሬዲዮ ላይ የተጀመረውን አዲሱን ዘመቻ በቸልታ አይመለከተውም።

መረጃ ሃይል ነውና አገራችን ውስጥ ፍትህ እንዲሰፍን፡ በመልካም አስተዳደር እጦት ሥር እየሰደደ የመጣው ድህነት እንዲቀረፍና ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር የሚሻ ዜጋ ሁሉ ወያኔ በሚዲያ ላይ የጀመረውን ጥቃት ለማስቆም ከጎናችን እንዲሰለፍ ግንቦት 7 የትግል ጥሪውን ያቀርባል።

ወያኔ በመረጃና ደህንነት መሥሪያቤቱ አማካይነት ያስተላለፈው የሰሞኑ ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ በተለይም በሰላማዊና ህጋዊ ትግል ወያኔን መቀየር ይቻላል በማለት አገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን የፖለቲካና የስቪክ ድርጅቶች መተንፈሻ ለማሳጣት ሆን ተብሎ የተቀነባበረ መሆኑን ህዝባችን እንዲረዳና በህዝባዊ እምቢተኝነት ሴራውን ለማክሸፍ መነሳት ጊዜው ግድ የሚል የወቅቱ አንገብጋቢ የትግል ጥሪ መሆኑን ግንቦት 7 የፍትህና የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያስገነዝባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የህወሃት ባለስልጣኖችና ቤተሰቦቻቸዉ ከፍተኛ የአገር ኃብት ወደ ዉጭ በማሸሽ ላይ ናቸዉ

የህወሃት ወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ከሃገር ውስጥ የዘረፉትን ሐብት ወደ ውጭ በማሸሽ ላይ እንደሚገኙ እና በሌሎች ሃገራት የተለያዩ የንግድ ስራዎች ላይ እየተሰማሩ እንደሆነ ባሳለፍነው ሳምንት የዜና ርዕስ ሆኗል።

የዜና ምምጮቻችን ባሳለፍነው ሳምንት መረጃውን ይፋ እንዳደረጉት የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት የሀገሪቱን ገንዘብ በተዘዋዋሪ በውጪ በሚኖሩ የስርአቱ አግልጋዮች ስም የቦታና የንግድ ግዢ በውጪ ሀገር የማድረግ ስራ በሰፊው እየሰሩ ነው። በተለይም በአሜሪካን ሀገር በሚገኙ የተለያዩ ግዛቶች በጉብኝት ስም ታማኝ ሰዎችን በመላክ የሀገሪቱን ገንዘብ በማሸሽ ቦታና የንግድ ማእከሎችን እንዲገዙ እየተደረገ ነው። ህወሃት ራሱ ያልተረጋጋ እና አደጋ ያንዣበበት በመሆኑ ውስጣቸው መረጋጋት እንደሌለበት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚወጡ መረጃዎች በማሳየታቸው እናም ስርዓቱ በቅርቡ ፈራሽ መሆኑን የተገነዘቡት በተለይም የህወሃት ከፍተኛ አመራሮች ይኼን ገንዘብ የማሸሸን ዘዴ እንደ አንድ አማራጪ ወስደው ራሳቸውንና ንብረታቸውን ለማሸሽ እየተዘጋጁ መሆኑ የሳምንቱ ዜና ሆኖ ሰንብቷል።

## ወያኔ ደቡብ ጎንደር ዉስጥ በትዕዛዝ ሰዉ አስገደለ

ባሳለፍነው ሳምንት በስፋት ከተዘገቡ ዜናዎች አንዱ ደግሞ በደቡብ ጎንደር ዞን ፎገራ ወረዳ አስተዳዳሪ ትእዛዝ አንድ ሰው መገደሉ እና ዘጠኝ ሰዎች መቁሰላቸው ነው።

በሃገር ቤት የሚታተመው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ እንደዘገበው በ2007 ዓመተ ምህረት የወያኔ አገዛዝ ለይስሙላ ለሚያካሂደው ምርጫ ማታለያ ይሆን ዘንድ በአማራ ክልል ለደጋፊዎቹ መሬት እያከፋፈለ የሚገኝ ሲሆን በደቡብ ጎንደር ዞን ፎገራ ወረዳ በህዝቡ እና በአገዛዙ መካከል ከፍተኛ አለመግባባት ተፈጥሯል። አለመግባባቱ እየጠነከረ በመጣበት ወቅት ሰሜ ከበደ የተባለው በወረዳው የወያኔ አገዛዝ አስተዳዳሪ በህዝቡ ላይ ተኩስ እንዲከፈት ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን በዚህም አንድ የ25 ዓመት ወጣት በሁለት ጥይት ተመቶ ተገድሏል። በወረዳው ህዝብ ላይ በተከፈተው የተኩስ እሩምታ ዘጠኝ ሰዎችም ከባድ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በአሁኑ ወቅት በአካባቢው ከፍተኛ ያለመረጋጋት የሰፈነ ሲሆን ወረዳው በወያኔ ታጣቂዎች መወረሩንም ዘገባው አካቷል።

# ዛሬ የሚያስፈራሯችሁን እስከ ዘላለሙ የማትሰሙበት ግዜ ይመጣልና አትፍሩ

ህወሃት የሚያራምደው የዘረኝነት ፖለቲካና፤ የተዘፈቀበት የሙስና አዘቀት ሊወጣ ከማይችልበት አዙሪት ውስት ከተውታል። ከእንግዲህ ወዲህ ለህወሃቶች የቀራቸው አንድ አማራጭ ብቻ ነው። ሁሉንም ዜጎች በዘረኝነት ሰንሰለት አስሮ ቀጥቅጦ እና አፍኖ መግዛት ቀጣዩ ቅዥታቸው ነው።

የዚህ አፍኖ የመግዛት ቅዥታቸው መገለጫም ዜጎች ህወሃት ስለሚፈፅመው ወንጀል ምንም ዓይነት መረጃ እንዳያገኙ ማድረግ አንዱ ነው። ህወሃት የሚፈፅመው ወንጀል ከህዝብ ዓይንና ጆሮ ተሠውሮ እንዲረሳ ይመኛል። ይሄን ምኞቱን እውን ለማድረግም ሌሎች ነፃ ሚዲያዎችን አሸባሪ ማለት ወይም ደግሞ ሌላ የተሰወረ አጀንዳ ያላቸው እያለ ማላዘንን ሥራየ ብሎ ተያይዘውታል። ከሰሞኑ አዲስ አበባ ውስጥ የሚታተሙ ስምንት የግል ህትመቶችን አሸባሪዎች በማለት ክስ መስርተዋል።አስቀድመው ፈርደው ከጨረሱ በኋላ ክስ መመሥረት የህወሃቶች የተለመደ የፍትህ ሥርዓት ነው። በአገሪቷ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ግዜ ከመንግስት ቁጥጥር ውጪ ሁኖ የተቋቋመውን ኢሳትንም አሸባሪ እያሉ ሰሚ አልባ ጩኸት እየጮኹ ነው። የኢሳት ቴሌቭዥንና ሬዲዮንን የሚሰማም በአሸባሪነት ይከሰሳል እያሉ በየዜጎች ደጅ እየተንከላወሱ ለማስፈራራት እየሞከሩ ነው።

እኛ ግን እንዲህ እንላለን !!! አትፍሩ ! አትፍሩ ! አትፍሩ ! ኢሳትን ሰምታችኋል ብሎ የሚያስፈራሯችሁን ለዘላለሙ የማትሰሟቸው ግዜ እየመጣ ነው። የነፃነት ጎህ ቀዶ ሁላችን የፈለግነውን ሰምተን፤ ያልፈለግነውንም የምንተውበት ዘመን እሩቅ አይደለም። ግንቦት ሰባት የፍትህ የነፃነት እና የእኩልነት ንቅናቄም የተቋቋመው ዜጎች ያለማንም ጣልቃ ገብነት የወደዱትን ወስደው፤ የጠሉትን መተው የሚችሉበትን መንገድ ለማመቻቸት ነው። ዘረኞቹ በደምና አጥንት ታውረው ጭካኔን ከጀግንነት ቀላቅለው እኛ ብቻ ወንድ ባሉበት መንደር ሌላ ጀግና ኢትዮጵያዊ ወንድ ገስግሶ የሚመጣበት ዕለት እየደረሰ ነውና እንዳትፈሩ እንመክራችኋለን። ህወሃቶች ዜጎችን ከሰው በታች አድርገው ለመግዛት እንዲመኙ ያደረጋቸው እብሪት የሚተነፍስበት ዘመን እሩቅ አይሆንምና አሁንም አትፍሩ።

ህወሃቶች ከእነርሱ ቁጥጥር ውጪ ያሉ ነፃ ሚዲያዎችን እንደማይታገሱ የታወቀ ነው። ለምን ቢሉ የወንጀላቸው ብዛት፤ የክፋታቸው ጥልቀት ሳይነገር ተሠውሮ እንዲቀር ስለሚመኙ ነው። ይህን ምኞታቸውን እውን ለማድረግም ራሳቸው የሠረቱን ህግ ውልቅልቁን አውጥተው ያፈራርሱታል። ዜጎች መረጃ የማግኘት መብት አላቸው ተብሎ እነርሱ "ህገ-መንግስታችን" እያሉ በሚጠሩት ላይ በማያሻማ ሁኔታ የተቀመጠ ቢሆንም እነርሱ ግን ለራሳቸው ህግ መታመንን አልመረጡም። እንዲያውም እነርሱ ሞተንለታል የሚሉትን ህግ አፈር አስገብተው ራሳቸው ህግ ሆነው ተፈጥረዋል። እነርሱ ህግ ሁነው በመፈጠራቸውም በየዜጎች ደጅ እየተንከላወሱ ኢሳትን ብትሰሙ ወዮላችሁ እያሉ ያስፈራራሉ። ዜጎች ግን የሞኝ ዘፈናቸውን መልሰው መልሰው ለሚያላዝኑ ኢሕአዴጋዊያን ዛቻ የሚንበረከኩ አይሆኑም። አገራቸውን በተመለከተ ማንኛውንም መረጃ ለመስማት ያላቸውን ነፃነትም ለምናምንቴዎች አሳልፈው የሚሰጡ አይሆኑም።

ጎሬቤታችን ኬኒያ ከአስር በላይ የግል ቴሌቭዥን ጣቢያዎች አሏት።በርካታ በአጭር ሞገድና በኤፊኤም ሞገዶች የሚተላለፉ ሬዲዮኖችም አሏት። የኬኒያ መንግስት ለዜጎቹ ክብርና ፍቅር ስላለው የተቻለውን ያክል ነፃ ሚዲያ እንዲኖር ይጥራል። ለህዝቡ ክብርና ፍቅር የሌለው ህወሃት ግን በወረቀት ላይ በፃፈው ህግ ዜጎች መረጃ የማግኘት መብታቸው ያልተገደበ ነው ቢልም በተግባር ግን የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት ያፍናል። ነፃ ሚዲያ እንዳይፈጠር ለማድረግ፤ የተፈጠሩትንም ለማጥፋት ግዜውንና የአገሪቷን ሃብት በከንቱ ያባክናል። ህወሃት ከድሃ ጉሮሮ እየነጠቀ ኢሳትን ለማፈን በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር አባክኗል። የአገሪቷ የህግ ተቋማትም ሌቦችንና ነፍሰ ገዳዮችን መከታተል ትተው በነፃነት እንፃፍ ብለው የተነሱ ጋዜጠኞችን በማሳደድ የአገሪቷን የሥራ ሠዓትና ሃብት በከንቱ ያባክናሉ። ህወሃቶች ይሄው ናቸው። አገር፤ ወገን፤ ህዝብ የሚባል ነገር በሂሊናቸው ያልተፈጠረ፤ እነርሱ ብቻቸውን ሌላውን ተጭነው መኖር የሚፈልጉ፤ የጨካኞችና የእብሪተኞች ስብስብ መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም።

የተከበራችሁ ያገራችን ዜጎች !

አገራችሁን በተመለከተ መረጃ ማግኘት የዜግነት መብታችሁ መሆኑን እንዳትረሱ። ይሄም እነርሱ "ህገ-መንግስት" ብለው በሚጠሩት ላይም በግልፅ ተቀምጧል። ይሄን በህግ ደንግጎ ሲያበቃ ኢሳትንና ሌሎችን ነፃ ሚዲያዎችን መስማት አትችሉም ሲል የማውቅላችሁ እኔ ነኝና የምትሰሙትንና የምታዩትን የምመርጥላችሁ እኔ ነኝ እያለ መሆኑን አስታወሱ። ይሄ ማለት አዋቂው እኔ እንጂ እናንተማ ክፉን ከደጉ ለመለየት ገና አልደረሳችሁም ማለት መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል። መንግስት ነኝ ብሎ በአገሪቷ ጫንቃ ላይ የተቀመጠው ህወሃት-ኢሕአዴግ ህዝቡን የማያከብር ብቻ ሳይሆን ለህዝብ ያለው ንቀትም ወሰን የሌለው ሁኗል። ይሄ ዘረኛና ዘራፊ ቡድን ክብራችንን አዋርዶና አንገታችንን አስደፍቶ ሊገዛን አይገባውም። ፍርሃት ይብቃ። ህወሃት እየፈጠረ ያለው ፍራቻን መሸሸ አይገባም፤ ይሄን ፍርሃት መጋፈጥ የጀግና ተግባር ነውና ለክብራችሁና ለነፃነታችሁ ስትሉ ፍርሃቱን ተጋፈጡት እንጂ አትሸሹት።

በዚያ በጨካኞች መንደር ሁናችሁ በሠላማዊ ትግል ብቻ ለውጥ እናመጣለን ብላችሁ የተደራጃችሁ የፖለቲካ ድርጅቶችም መረጃ የማግኘት፤ መረጃ የመሰብሰብ እና የማሰራጨት መብታችሁ ነው ብለን ልንነግራችሁ አንዳዳም። በነፃ ሚዲያ መናገርም ሆነ ለማንኛውም ሚዲያ መረጃ የመስጠት ማንም የሚሰጣችሁ መብት እንዳልሆነ ታውቃላችሁ። እኛ እንደምንገምተው ኢሳትም ሆነ ሌሎች ነፃ ሚዲያዎች የእናንተም ሃብት ናቸው። ህወሃት-ኢሕአዴግ አትስሙ ወይም ደግሞ አትናገሩ ሲላችሁ ያንን የእብሪተኛ ትዕዛዝ አለመቀበላችሁን ለነፃ ሚዲያዎች መረጃ በመስጠትና ሃሳባችሁን በነፃው ሚዲያ በመግለፅ እምቢተኝነታችሁን በማሳየት ለምትመሩት ህዝብ አርአያ እንድትሆኑ ብናሳስባችሁ ደፈሩን እንደማትሉ ተስፋ እናደርጋለን። ከዚህ አንፃር ሰማያዊ ፓሪትና አንድነት ያወጡትን መግለጫ በአድናቆት የምንመለከተው መሆኑን ለማስታወቅ እንወደላን።

ለህወሃት-ኢሕአዴጎች !

ራሳችሁን ከአሸባሪ ምግባርና መዝገብ ማስፋቅ ሳትችሉ የነፃነት ፍላጎት ያላቸውን ሁሉ አሸባሪ እያላችሁ ማላዘናችሁን የምታቆሙበት ግዜ እየመጣላችሁ ነው። እናንተ ከላይ ሁናችሁ ህዝቡ ከሥር ሁኖ እናንተን ተሸክሞ ለዘላለም እንደማይኖር አበክረን ልናሳውቃችሁ እንወዳለን።በየሰው ደጅ ካድሬዎቻችሁን ልካችሁ ኢሳትን አትስሙ እያላችሁ የማስፈራራት እብሪታችሁ ረገብ የሚልበት ግዜ እየመጣላችሁ ነው። ዛሬ ህዝባችንን የእኛን ብቻ ስሙ፤ የእነርሱን አትስሙ ማለታችሁ ለህዝባችን ያላችሁን ንቀት የሚያመላክት ነው። ህዝባችንን እንደናቃችሁና እንዳዋረዳችሁ አትቀጥሉም። የነፃነትን ፍላጎት አፍናችሁ አታቆሙትም። የፍትህ ጥማታችንን በአፈሙዝ ልትገቱት አትችሉም። የእኩልነትን ጥያቄ በውሸትና በዛቻ አታዳፍኑትም።

እውነት እውነት እንላችኋለን ወንጀላችሁ ሳይነገር፤ በስውር የዘረፋችሁት በአደባባይ ሳይገለጥ አይቀርም። እኛም ቀንና ማታ ለዚያ ግብ ሳናገራግር እየሰራን ነው። በአገራችን የነፃነት ጎህ ሳይቀድ ለሸፋሸፎቶቻችን እንቅልፍ፤ ለስጋችንም ዕርፍት አይሆንም። የዘረኞችና የዘራፊዎች ጀንበር ሳትጠልቅ፤ የእኩልነት ናፋቂዎች ጎህ ሳትቀድ አናርፍም። ያነገታችሁት መሣሪያ የሸንበቆ ምርኩዝ እስከ ሚሆን የጀመርነውን ትግል ዕለት ዕለት እያጎለበትነው እንቀጥላለን።

ህወሃት-ኢሕአዴጎች ሆይ ስሙ! ይሄን ህዝብ ከሚችለዉ በላይ ገፍታችኋታል። ህዝቡም ሊሸከማችሁ ከሚገባ በላይ ተሸክሟችኋል።እንዲህ ህዝባችንን መፈናፈኛ አሳጥታችሁ እና እስከ ልጅ ልጆቻችሁ ረግጣችሁ ለመግዛት ያለማችሁት ህልም በህልምነቱ ብቻ እንደሚቀር ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ አይግባችሁ። ትግላችን ጥሩ መሠረት ይዟል። ከዚህ በኋላ ወደ ኋላ የሚመልሰን ምድራዊ ኃይል የለም። እውነት እውነት እንላችኋለን ለዘላለም ኢትዮጵያዊያንን አዋርዳችሁ የመግዛት ህልማችሁ ቅዥት መሆኑን ደግመን ልንነግራችሁ እንወዳለን።

በህወሃት-ኢሕአዴግ ውስጥ ሁናችሁ የነፃነት፤ የፍትህ እና የእኩልነት ጥያቄያችንን የምትጋሩን ወገኖቻችን እስከ አሁን የምታደርጉት የውስጥ ትግል ፍሬ እያፈራ ነው። ፍሬውን በራሪ ወፍ እንዳይለቅመው የተለመደው ጥንቃቄ እንዳይለያችሁ ይሁን። አሁን ህዝቡ መረጃ እንዳያገኝና፤ መረጃ እንዳይሰጥ የሚሞከረው ሙከራ ህገ-መንግስት ተብየውን የሚጥስ መሆኑን ታውቃላችሁ። ይሄን ካድሬው ሁሉ እንዲገነዘበው የውስጥ ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ራሱ ያወጣውን ህገ መንግስት አፈራርሶ ከትቢያ የሚቀላቅል ቡድን በምን ሞራል ብቃት ነው ሌላውን ህገ-መንግስቱን ሊንዱ ነበር እያለ የሚከሰው? በኢትዮጵያዊያን ላይ የተጫነው ህገ-መንግስት በህወቶች ሲፈርስ ትክክል ፤በሌላው በተግባር እንዲውል ሲጠየቅ ደግሞ ስህተት ሁኖ በአሸባሪነት የሚያስከሥሥ መሆኑን ግንዛቤ መጨበጥ ይጠቅማል።

በመጨረሻም በህወሃት-ኢሕአዴግ የጭቆና ቀንበር ሥር ለምትንገላቱ ወገኖቻችን ሆይ! አትፍሩ። ይህን የሚያስፈራራችሁን አካል እስከ መጨረሻው የማትሰሙበት ዘመን እየመጣ ነው። አሁን ፍርሃታችሁን ግደሉት። የምትሰሙትንና የምታዩትን እኔ ነኝ የምመርጥላችሁ ከሚል እብረተኛ እጅ ራሳችሁን ለማላቀቅ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ እያደረገ ያለውን የነፃነት፤ የፍትህና የእኩልነት ትግል ተቀላቀሉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## መሬታችንን ለባዕዳን አትስጡብን ያሉ ኢትዮጵያዉያን ገበሬዎች በወያኔ ፖሊሶች ተደበደቡ

መሬታቸው ለሕንድ የሻይ ልማት ኩባንያ መሰጠቱን በማውገዝ የተቃወሙ ኢትዮጵያዊያን በቅጥረኛ የወያኔ አገዛዝ ዘቦች ከፍተኛ ድብደባ የተፈጸመባቸውም በዚህ ሳምንት ነው።በጋምቤላ እና በሸካ አዋሳኝ ክልል መካከል ከሚገኘው ቦታ ከ3 ሺህ ሄክታር የሚበልጥ ጥብቅ ደን መሬት ተመንጥሮ ለሻይ ልማት እንዲውል ቨርዳንት ሃርቨስት አግሮ ኢንዱስትሪ በመባል ለሚታወቅ የህንድ ኩባንያ ተሸጧል። በመሬቱ ዙሪያ ከ100 ሺህ የሚበልጡ የአካባቢው ነባር የቀድሞ ነዋሪዎችም የነበሩ ሲሆን ይህንን ህገወጥ ተግባር በመቃዎማቸው ምክንያት በወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ በደል እንደደረሰባቸው ሃገር ውስጥ ለሚታተመው ሰንደቅ ለተሰኘው ጋዜጣ አስታውቀዋል። ነዋሪዎቹ በከብት እርባታ፣ የማር ልማት እና በተለያዩ መንገዶች ከጥብቅ ደኑ ተጠቃሚ የነበሩ ሲሆን የአካባቢውን አየር ንብረት የተዛባ እንዳይሆን ደኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኝ እንደነበረ እና ይህ ጉዳይ ሳይጤን በግብታዊነት ተመንጥሮ ለህንድ ሰዎች እንዲሸጥ መደረጉን በከፍተኛ ሁኔታ ተቃውመዋል። የወያኔ አገዛዝ ይህንን ተቃውሞ ያሰሙ የአካባቢው ዜጎችን እያደነ ከፍተኛ ስቃይ እና ድብደባ እንደሚፈጽምባቸውም ተናግረዋል።

## ህወሀቶች ሃት ወደ ውጪ ሀገር በመሄድ የንግድ ድርጅት በግለሰብ ደረጃ እየገዙ ነው ተባለ

የህወሃት ባለስልጣኖኖች ከፍተኛ የአገርና የህዝብ ገንዘብ ይዘዉ ወደ ዉጭ አገር እየሄዱ ንብረት እየገዙ መሆኑን አባይ መድያ አጋለጠ።የኢትዮጵያ መንግስት የሆነው ህወሃት በሀገራችን ሰላምና ፍትህ፣ ልማትና እድገት እየመጣ ነው እያለ የተረጋጋ መሆኑን በማስመሰል በየጊዜው ይናገራል። ነገርግን የሀገሪቱን ገንዘብ በተዘዋዋሪ በውጪ በሚኖሩ የስርአቱ አግልጋዮች ስም የቦታና የንግድ ግዢ በውጪ ሀገር የማድረግ ስራ በሰፊው እየተፋፈመ መሆኑን የውስጥ ዜና ምንጮቻችን ገልፀዋል። በተለይም በአሜሪካን ሀገር በሚገኙ የተለያዩ ግዛቶች በጉብኝት ስም ታማኝ ሰዎችን በመላክ የሀገሪቱን ገንዘብ በማሸሽ ቦታና የንግድ ማእከሎችን እንዲገዙ እየተደረገ ነው። ህወሃት ራሱ ያልተረጋጋ እና አደጋ ያንጃበበት በመሆኑ ውስጣቸው መረጋጋት እንደሌለበት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚወጡ መረጃዎች ያሳያሉ። ታዲያ ይህንን ፍርሃት በመሸፈን በበላይነት የህወሃት ኤፈርት ከፍተኛ አመራሮች ይኼን ገንዘብ የማሸሽን ዘዴ እንደ አንድ አማራጪ ወስደው ራሳቸውንና ንብረታቸውን ለማሸሽ እየተዘጋጁ ነው ሲል መረጃውን የላከልን ዘጋቢያችን አስታውቋል። በቅርቡ ከሁለት ወር በፊት የኤፈርት ልኡክ ቡድን ወደ አሜሪካ ተልእኮ እንደነበርም አስረድቷል። ከዚህ ዜና ጋር በተያያዘ የህወሃት ባለስልጣኖች ገንዘባቸውን በማሸሽ ላይ ናቸው ሲል የግንቦት 7 ሬዲዮ በቅርቡ መዘገቡ ይታወሳል።

## በኦሮምያ ዉስጥ ወረቀት በትናችኋል የተባሉ ወጣቶች ከየቤቱ እየታደኑ ታሰሩ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በኦሮሚያ ክልል የሚያካሄደዉን የእስርና የእንግልት ዘመቻ በመቀጠል በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች ወረቀት በትንችኋል ያላቸዉን ወጣቶችና ተማሪዎቸ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ አስሮ እያሰቀየ መሆኑን የአፍሪካ ቀንድ የሂውማን ራይትስ ሊግ ለኢሳት ሬድዮና ተሌቪዥን በላከው መግለጫ ይፋ አደረገ። ከነሐሴ እስከ ታህሳስ ባለው አራአት ወር ጊዜ ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ ፌደራሊስት ኮንግረስ አባላት ናቸው የተባሉ 45 ሰዎች በጉጂ ዞን በነገሌ እስር ቤት ውስጥ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ታስረው የሚገኙ ሲሆን ከታሰሩት መካከልም የሁለተኛ ደረጃ፣ የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና መምህራን እንደሚገኙበት ታዉቋል።

በጉጂ ወረዳ በሀርኬሎ ከተማ የሚኖሩ 8 የኮሌጅ ተማሪዎች የጉጂ ኦሮሞዎች መብት እንዲከበር የሚጠይቁ በራሪ ወረቀቶችን በከተማዋ ውስጥ በመበተናቸው መታሰራቸውን የገለጸው ሊጉ፣ ጎበና ገመዳ የተባሉትን የሁለተኛ ደረጃ መምህር ጨምሮ ጋልጋሎ ጩሉኬ፣ ኮራራዩ ካንክ፣ ኢጀርሳ ሻቆ፣ ናኖ ቻማሪ እና ዙሜ ሻንቆ እስከዛሬ በእስር ላይ ይገኛሉ። በቡሌ ሆራ ዞን በአዶላ ፖሊስ ጣቢያ ደግሞ የኦሮሞ ፌደራሊስ ኮንግረስ አባላት የሆኑት የፓርላማ አባሉ ቦረና ጃኖ፣ ፣ ሂርባየ ጋልጋሎ እና ኡቱራ አዱላ ካለፉት 3 ወራት ጀምሮ ታስረው ይገኛሉ። የሰብአዊ መብት ሊጉ መንግስትና አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ለችግሩ ትኩረት በመስጠት ግለሰቦቹ እንዲፈቱ ጥረት እንዲያደርጉ ጠይቋል።

በተመሳሳይ ዜና ደግሞ በዳውሮ ዞን በማረቃ ወረዳ የዛሬ ዓመት ገደማ ከዲሳ ህዝብ የወረዳ ማዕከል ጥያቄ ጋር በተያያዘ ‘የህዝቡ የወረዳዉ ማዕከል አያማክለኝም ጥያቄ ተገቢ እና ወቅታዊ በመሆኑ መፍትሔ ሊሰጠዉ ይገባል’ በማለት በገሳ ከተማ ላይ በተደረገዉ የሎማ ወረዳ የ መንግሥት ሠራተኞች ስብሰባ ላይ በመናገራቸው ምክንያት የ3 ዓመት ከ6 ወር እስራት የተፈረደባቸው በዳዉሮ ዞን ታርጫ ማረሚያ ተቋም የእስራት ጊዜያቸውን ሲከታተሉ የነበሩት ሳጂን ሽታዬ ወርቁ በታሰሩት ማረሚያ ቤት ሊገኙ አለመቻላቸውን ቤተሰቦቻቸው ተናግረዋል። ሳጂን ሽታየ በእስር ቤት በከፍተኛ ሁኔታ በመደብደባቸው ራሳቸውን ለሁለት ቀናት ያህል ስተው እንደነበር ቤተሰቦቻቸው ተናግረዋል።

የሳጂን ሽታዬ ወርቁ የቅርብ ዘመዶች እንደገለጹት ግለሰቡ ‘በታርጫ ማረሚያ ተቋም መታረም ስለማይችል ወደ ጋሞ ጎፋ ዞን ሳዉላ ማረሚያ ተቋም በዝዉዉር ተልኳል ቢባልም፣ ሳዉላ እስር ቤት ውስጥ ሊያገኙዋቸው ባለመቻላቸው ግለሰቡ በህይወት ይኑሩ አይኑረ ለማወቅ መቸገራቸውን በጭንቀት ገልጸዋል።

የሎማ ዲሳ ህዝብ የወረዳ ማዕከል ጥያቄ እስከዛሬ ድረስ ምላሽ ያላገኘ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ከጥያቄዉ ጋር በተያያዘ ከ30 የሚበልጡ የአካባቢዉ ተወላጆችና ሽማግሌዎች በተርጫ ማረሚያ ቤት ታስረዉ እንደሚገኙና በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የአካባቢዉ ነዋሪዎች ቀዬአቸዉን ለቀዉ ተሰደዋል።

## ወያኔ ለ2007ቱ ምርጫ የመንግስት ሰራተኞችን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

“ሰራተኞቹ በዝቅተኛ ክፍያ ተንገላቱ፣ በየጊዜው ስራ ለመልቀቃቸውም ዋናው ምክንያት ይኸው ዝቅተኛ ደመወዛቸው ነውና የመሳሰሉትን የአዞ እንባዎች ከፋሽስት ወያኔ መስማት ከሹፈት በላይ ነው” የሚሉ ጥቂት አይደሉም።

ስለሆነም ያሁኑ የደመወዝ ጭማሪ ወሬም በመቶ ሽዎች የሚቆጠረውን የኢትዮጵያ ሰራተኛ ክፍል በዚህ ሊሆን ላይሆን በሚችል የደመወዝ ጭማሪ ሰበብ ለወያኔ የውሸት ምርጫ አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርግ ለማባበል ሆን ተብሎ በዚህ ሰአት የተለቀቀ ፕሮፓጋንዳ እንደሆነ የሚገልጹ ወገኖች ተበራክተዋል።

ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚና በተመሳሳይ ሁኔታ ገበሬውን በማዳበሪያና ምርጥ ዘር አቅርቦት ከተሜውን ደግሞ በኮንዶሚኒየም ቤት ግንባታ ሰበብ በስሩ አቅፎ እንደፈለገው ለማሽከርከር ሲሞክር የነበረው በዚሁ ይስሙላ ምርጫ ዋዜማ እንደነበር አይዘነጋም። ከዚህ በፊት በነበሩት የዜና እወጃችን እንደገለጽነውም በአዲስ አበባና በሌሎችም የሀገራች ክፍሎች የሚገኙ ጥቃቅን ተቋማት የሚባሉትንና የሴቶችና ወጣቶች ፎረሞችን፣ እንዲሁም ሌሎች የወያኔ ዝቅተኛ አመራሮችን ጨምሮ አመለካከታቸው ያልጠራ የሚባሉትን ተቃዋሚ ናቸው የሚባሉ ሰራተኞችን በሙሉ በተለያዩ አደረጃጀቶች ሰበብ ለቀጣዩ ሀገራዊ ምርጫ አጋዥ እንዲሆኑ ለማድረግ ፋሽስት ወያኔ ገና በጠዋቱ የተግባር እንቅስቃሴ እነደጀመረ መግለጻችን ይታወሳል።

## ወያኔ ቀጣዩን ምርጫ በሥልጠና ስም የግል

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

“የሃይማኖት አክራሪነትና ሽብርተኝነት ዋናው ምንጭ ድህነትና ተስፋ መቁረጥ ነው” በማለት ፕሮፓጋንዳቸውን የሚነዙት የዚሁ ስልጠና መሪ ወያኔዎች፤ እያወሩት ላለው ድህነት ሃላፊነት በመውሰድና ተገቢውን የእርምት እርምጃ በማዘጋጀት መፍትሄ መፈለግ ያለበት ባለቤቱ ወያኔ መሆኑን ዘንግተው በድህነት ምክንያት ተስፋ የቆረጠ ሕዝብ ወደ ሽብር ይሄዳል በማለት በድክመታችን ሊቀልዱብንና በሀይማኖት አክራሪነት ሰበብ ምስኪኑን ምእመን በማንገላታት ላይ ይገኛሉ” የሚሉ ወገኖች የሃይማኖትም ሆነ ሌላ አክራሪነት በሀገራችን የለም ድህነታችንም ቢሆን ከወያኔ ጋር የመጣ ነው ወያኔ ሲተፋም አብሮ ያጠፋል ይላሉ። ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ምክንያቶችን በመጠቀም ሕዝብን በጸረ ሽብር ዘመቻ ስር ለማሰለፍ ቢሞክርም ጥረቱ ብዙም እንዳልሰመረለትና እንዲያውም ሕብረተሰቡ ከወያኔ ውጭ ሽብርተኛ የሚባል ነገር የለም በማለት በግልጽ እስከመናገር መድረሱ ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ወያኔ በሶማሊያ ክልል 47 ሰዎች መግደሉ ተሰማ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ወያኔ እንዲህ አይነት ጥያቄ የጠየቀዉን ቀርቶ በተደጋጋሚ እጅ ያልነሳዉን ህዝብም የሚገድል አዉሬ ነዉ ያሉት እኚሁ ባለስልጣን በሶማሌ ክልል የብዙ ሰዎች ደም ሊፈስስ እንደሚችል ተናግረዋል። ባለስልጣኑ ንግግራቸዉን በመቀጠል በቀላፎና በአካባቢ የሚኖረዉ ህዝብ በተደጋጋሚ እርምጃ ሲወሰድበት እንደነበር አውስተው ፣ በቅርቡ የተወሰደው አስከፊ እርምጃ ግን በቀድሞወ ደቡብ አፍሪካ እንሰማው የነበረ እንጅ በአገራችን ላይ የሚፈጸም ነው ብሎ ለማመን ያስቸግራል ብለዋል።

ባከፍ ድር እየተባለ በሚጠራው ትምህርት ቤት ላይ እና በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ በተከፈተው ተኩስ ኡመር ሀጂ ሙሀመድ፣ ሙኒየር አዳቢ ሙሀመድ፣ ካሊድ ሙሀመድ አብዲ፣ ሀሰን አሊ ቤላህ፣ ወ/ሮ ሀሺ ሃጅ መሀመድ፣ ማዴቦ ሞሀመድ አብዲ፣ ሀጂ ኑሩ ሙሀመድ፣ ማዴባ ሞሀመድ አብዲ፣ መሀለም ካልየ ደውሀሊ፣ አብረሳ አደም ሞሀመድ፣ ሀጂ ኑሩ ሙሀመድ፣ ሞርየ ሞሀመድ ካር፣ ጋለው አብዲ የኑስ፣ የሱፍ ረምሳ አደም፣ ካሊባን ሳራህ ኡመርነህ፣ ኡስማን አብደሌ፣ ጠኒ ሙሀመድ ጣር፣ መንሲን ሙሀመድ ጣር፣ ደልግ አሊ ኡመር፣ ካሊድ ሙሀመድ አብደሌ፣ ሀሰን ማሌ አብዱላሂ፣ የሱፍ የሄ፣ ጀማል ኡመር ጠባህ፣ ሙሀመድ ኡስማን ጦለቤ፣ አህመድ መሀመድ፣ አሊ ቀሲም ቀለኔ፣ ባቡል ዳኑር፣ ከሬ ባዴ፣ ማን አረየ ባዴ፣ ጦርየ አዊ ባዴ፣ አብዲ ሸክለሌ፣ አሊ ኡስማን ቀለሌ፣ ሊሞ አሌባዴ፣ ማዲህ አብዱልኑር፣ ዙቅ ኡር እና የሌሎች የ12 በትተጨማሪ ሚኞች ስም ዝርዝር ቀርቧል።በአካባቢው የተነሳው ውጥረቱን ተከትሎ በትናንትናው አለት ደግሞ ተጨማሪ ሀይል ወደ አካባቢው መጓዙን ሽማግሌዎች ገልጸዋል።ክልሉን ከጀርባ ሆነው የሚያንቀሳቅሱት ጄኔራል አብርሀ በክልሉ ለሚፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ መሆናቸውን የአካባቢው ሰዎች ይገልጻሉ።

## የኢትዮጵያ አርሶ አደር በወያኔ ላይ አይነሳም

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በሌላ በኩል በረከት ሰምኦን በዚሁ ስብሰባ ላይ “30 በመቶ የሚሆነውን ወጪ የምንሸፍነው በውጭ እርዳታ በመሆኑ፣ ከውጭ ተጽእኖ ለመላቀቅ ወጪያችንን የሚሸፍን ገቢ ማግኘት አለብን” ሲል የተደመጠዉ አቶ በረከት፣ “በ1997 ምርጫ ወቅት የውጭ ሃይሎች ጥፋት ያጠፉትን መሪዎችን ወደ ፍርድ ቤት የምትወስዱዋቸው ከሆነ እርዳታ እናቆማለን ባሉት መሰረት እርዳታ አቁመውብን ነበር” ሲል ለብዙ ግዜ ደብቆት የቆየዉን ፀሐይ የሞቀዉ ሚስጢር ለወያኔ/ኢህአዴግ ባለስልጣኖች መናገሩ ተሰማ።

ከዚህ በተጨማሪ በ1984ቱ ድርቅ ጊዜ የአሜሪካ የእርዳታ ድርጅት ሃላፊ የመሬት ፖሊሲያችሁን ካልቀየራችሁ እርዳታ አንሰጥም ብለዋቸው እንደነበር ተናግሯል።ኢህአዴግ ከዋናዎቹ አመራሮች ጀምሮ በተዋረድ ለሌሎች አመራሮችም ምርጫውን ስለሚያሸንፉበት ሁኔታ ስልጠና እየሰጠ ነው። ኢህአዴግ የገጠሩን ድምጽ ሙሉ በሙሉ እንደሚያገኝ አቶ በረከትና ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ ተማምነዋል። ይሁን እንጅ የኢህአዴግ ካድሬዎች በየገጠሩ በመዞር ያልተደራጀውን አርሶአደር በአንድ ለአምስት በማደራጀት፣ በመሬት እጥረት የተከፋውን ወጣት የወል መሬት እየሸነሸኑ በመስጠት ላይ መሰማራታቸውን የሚደርሱን መረጃዎች ያመለክታሉ።

## ኢህአዴግ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መመሪያን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ችግራችንን እንፈትሽ የሚል” አቋም ሲይዝ ፣ ሌላው ወገን ደግሞ ዋናው ችግራችን ሻዕቢያ በመሆኑ በቅድሚያ ሻዕቢያን እንውጋ የሚል አቋም ይዞ እንደነበር፣ እና ሻእቢያን ከወጋን በሁዋላ ወደ ውስጥ ችግራችን እንመልከት የሚለው ሶስተኛው አማራጭ አሸንፎ መውጣቱን ገልጿል።በ1997 ዓም ዋናው የአመጽ ሀይል የነበረው ስራ ያጣውና ተስፋ የቆረጠው ወጣት ነው በማለት የገለጹት አቶ በረከት ለወጣቱ ስራ ካልተፈጠረለት በመንግስት እና በአገር ላይ እንደሚያምጽ ገልጸዋል። መንግስት የምርጫ 97ትን አመጽ ያስነሱት ተቃዋሚዎች ናቸው ብሎ ሲከስ መቆየቱ ይታወቃል።

ኢህአዴግ ከባላሀብቱ ነጻ የሆነ መንግስት ለመመስረት መነሳቱን የገለጹት አቶ በረከት፣ ስልጣን ላይ የሚያመጣን አርሶአደሩና በከተማ ያለው ጭቁኑ ህዝብ ነው እንጅ ባለሀብቱ አይደለም ብሏል። የኢትዮጵያ መንግስት በባለሀብቱ ገንዘብ የሚተዳደር አይደለም ያሉት አቶ በረከት፣ ገንዘብ ከፈለገ ከባላሀብቱ በግብር መልክ መውሰድ እንደሚችል በመናገር የወያኔ ዋናዉ አላማ ህዝብና አገር ሳይሆን ስልጣንና ገንዘብ መሆኑን ሳያፍር አፉን ሞልቶ ተናግሯል። ይህ መንግስት ለህልውናው የራሱ የገቢ ምንጭ እንዳሉት የተናገረዉ አቶ በረከት፣ አየር መንገድን፤ ባንኮችንና መብራት ሀይልን በምሳሌነት አንስቷል። የመንግስትን አስተዳደር ያለምንም ችግር ለማስኬድ የባለሀብቱም የውጭ ድጋፍም እንደማያስፈልግ በረከት አክሎ ተናግሯል።

በረከት ስምኦን መንግስት በቂ ገንዘብ አለዉና የሚቀጥለዉን ምርጫ ኢህአዴግ ያለባለሀብቶች ድጋፍ ማሸነፍ እንደሚችል በተናገረበት ወቅት “በቂ ገንዘብ” አለን ማለቱ ብዙዎቹን ተሰብሳቢዎች ማስገረሙን ስብሰባውን የተከታተሉት አንድ ከፍተኛ የኢህአዴግ አመራር ገልጸዋል። እንደ ባለስልጣኑ አባባል ኢህአዴግ ለምርጫ ማስኬጃ ከመንግስት ገንዘብ እንደሚወስድ የበረከት ንግግር በቂ ማሳያ ነው ።መንግስት የራሱ ገንዘብ ከሌለው እንደምእራብ አፍሪካ አገሮች አንሆናለን ብለዉ ያሾፉት እኚሁ ባለስልጣን የኮትዲቩዋር ሚኒስትሮች ደሞዛቸውን የሚወስዱት ኮትዲቯር ከሚገኘው የፈረንሳይ ኢምባሲ እንደሆነ ተናግረዋል።